## የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በገጠር ኢነርጂ ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች እና የፈጠራ ስራ ባለቤቶችን አወዳድሮ መሸለም ይፈልጋል፡፡

## በመሆኑም ለተወዳዳሪዎች በተላለፈው ማታወቂያ ተወዳዳሪዎች የሚሞሉትን ፎርም

## የማመልከቻ ቅጽ

<u>ስለ ፕሮግራሙ አጭር ማብራሪያ</u>

የኢትዮጵያ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከውሃ፣ የመስኖና የኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በግሎባል ኢንቫይሮንሜንት ፋሲሊቲ (GEF) የገንዘብ ድጋፍ ለቤት ውስጥ ፍጆታና ለማምረቻ አገልግሎት የሚሆን ቀጣይነት ያለው የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ማበረታቻ ፕሮጀክት - ኢትዮጵያ፤ የሚል ፕሮጀክት እየተገበረ ይገኛል፡፡

ፕሮጀክቱ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን የሚጠቀሙ እንዲሁም የአፍላሽ/የግሪን ሃውስ/ ጋዝ ልቀታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ተበረታትተውና አድገው አሁን ያለውን ከቅሬተ-አካላት በሚገኝ ነዳጅ እንዲሁም“ቀጣይነት በሌለው ሰብስብ ሕይወት ላይ የተመሰረተውን የኃይል አጠቃቀም እንዲተኩ በማድረግ፤ ከኢነርጂ ጋር በተገናኘ የኢትዮያን የካርቦን ዳይኦክሳይድ ልቀት መጠን በሁለት ሚሊዮን ቶን ያህል ለመቀነስ ያለመ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በተለይም የገጠሩ ማህበረሰብ በታዳሽ ኃይሎች ላይ የተመሰረቱ ቴክኖሎጂዎችን ለቤት ውስጥ ፍጆታና ለማምረቻ አገልግሎት አብልጦ እንዲጠቀም የሚያበረታታ ነው፡፡ በግምት 200,000 በሚሆኑ አነስተኛ የፀሃይ ፒቪ እና 600,000 ያህል የተሻሻሉ የማብሰያ ምድጃዎች ላይ መዋዕለ ንዋይ እንዲፈስስ በማስቻል በግምት ስምንት መቶ ሺህ የሚሆኑ አባወራዎች (4 ሚሊዮን ሰዎች) በዚህ ፕሮጀክት አማካይነት ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

ከዚህም አንፃር ለገጠሩ ማህበረሰብ እንዲሁም ለንግድ ድርጅቶች ለማሞቂያ፣ ለመብራትና ለማምረቻ አገልግሎቶች ተስማሚ የሆኑ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን የሚያመርቱና የሚያቀርቡ ድርጅቶች ዕድገት፤ የዚህን ፕሮጀክት አላማዎች ከዳር ለማድረስ ቁልፍ እርምጃ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ፕሮጀክቱ የግሉን ዘርፍ ያሳተፈና ገበያ ተኮር የሆነ አቅጣጫን በመከተል

አላማውን ከግብ ለማድረስ ይጥራል፡፡ በዚህም መሰረት ፕሮጀክቱ ተወዳድረው ለሚያሸንፉ ኢንተርፕራይዞች የገንዘብ ሽልማት (ለመነሻ የሚሆን)፣ በዓይነታቸው ልዩ የሆኑ ስልጠናዎችንና የቢዝነስ ልማት አገልገሎቶችን በመስጠት የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ እድገትን ለማገዝ አቅዷል፡፡

የዚህ ሽልማት አላማ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ውስጥ በገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ዙሪያ እየሰሩ የሚገኙ ወይም በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉ የገጠር ኤነርጂ ቴክኖሎጂና የቢዝነስ ሞዴሎችን እና የፈጠራ ሥራ ባለቤቶችን ለማገዝና ወደፊትም ተመሳሳይ አዳዲስ ተቋማት እንዲፈጠሩ ለማበረታታት ነው፡፡

☐ የፀሃይ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ

☐ የተሻሻለ የማብሰያ ምድጃ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ

☐ የነዳጅ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ

☐ የነፋስ ሃይል የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ

☐ የባዮጋዝ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ

☐ አነስተኛ የሃይል **ስርጭት መረብ** (ሚኒ-ግሪድ) የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ

☐ ለገጠሩ ማህበረሰብ የኢነርጂ/የሃይል አጠቃቀም ውጤታማነት የሽልማት ዘርፍ

- **ትኩረት የተሰጠባቸው የውድድር ምድቦች አንዱን ይምረጡ**

- **የሚወዳደሩበት የውድድር ዓይነት /አንዱን ብቻ ይምረጡ/ ከመረጡ በኋላ በተዘጋጀው ወይም ለውድድር በአማራጭነት በተዘጋጀው ፕሮፖዛል ፎርማት መሰረት አንዱን አማራጭ ብቻ ሞልተው ይላኩ፡፡**

☐ **<u>የውድድር አማራጭ 1፡</u>** የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ፈጠራ ብቻ

☐ **<u>የውድድር አማራጭ 2፡</u>** የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የንግድ ስራ ሞዴል ፈጠራ ብቻ

*✍ ማሳሰቢያ ፎርሞችን ሲጠቀሙ 12 ፒክሰል እና በስንኞቹ መሐል 1.5 ክፍተት ይጠቀሙ በተጨማሪም የሚያዘጋጁት ፕሮፖዛል ከ 10 ገፅ መብለጥ አይኖርበትም፡፡ ሎሎች ማመሳከሪያ ሰነዶችን (ለምሳሌ የፋይናንስ፣ ሰርተፍኬት፣ ፓተንት፣ እና ሌሎችን ከ10 ገፅ የማይበልጥ ያያይዙ፡፡*

- **አጠቃላይ የአመልካች (በንግድ ተቋም/በግለሰብ) መረጃና ፕሮፋይል**

1. የተወዳዳሪው ዝርዝር መግለጫ በመጨረሻ ገፅ "ማሳሰቢያ" ስር ለውድድሩ የሚሆን አስፈላጊ ሰነዶች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ እና እንዲያያይዙ ማድረግ፡፡

2. የሚወዳደሩበት ሁኔታ
   - ☐ የግል
   - ☐ ጥምረታዊ
   - ☐ አክሲዎን
   - ☐ መንግስታዊ ያልሆነ (NGO)
   - ☐ መንግስታዊ ድርጅት

3. የአመልካች መረጃ
   3.1. የግል ወይም የተቋም ባለቤት ተወዳዳሪዎች ሙሉ መረጃ

ሙሉ ስም፡- ____________________________________________

ፆታ፡- __________________________________ ዕድሜ፡- ______________________________

የትምህርት መስክ፡ - ____________________________________________________________

የትምህርት ደረጃ፡ - ____________________________________________________________

የስራ ሀላፊነት፡-_______________________________________________________________

ኢ-ሜይል፡-____________________________________________________________________

የቢሮ ስልክ ቁጥር፡-_____________________________________________________________

የሞባይል ስልክ ቁጥር፡-__________________________________________________________

የፖስታ ሳጥን ቁጥር፡-____________________________________________________________

ዌብሳይት (ካለ)

________________________________________________________________

ከተማ/የገጠር ዞን፡-_______________ ወረዳ፡-________ ቀበሌ፡-______ የቤት ቁጥር፡-______

3.2. በድርጅት በኩል ለሚያመለክቱ ተጨማሪ መሟላት ያለባቸው መረጃዎች

የድርጅቱ/የተቋሙ ስም፡-______________________________________________________

የድርጅቱ/ተቋሙ ርዕይ ወይም ዓላማ፡-

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

የታደሰ የንግድ ምዝገባ ቁጥር፡-____________________________________________________

ድርጅቱ ሲቋቋም የነበሩ የሰራተኞች/የአባላት ብዛት፡-______________________________________

የድርጅቱ/ተቋሙ ውስጥ የሚሰሩ የሰራተኞች ብዛት፡-_______________________________________

ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓመተ ምህረት፡-_____________________________________________

4. የሽልማቱ ጥቅል

አሸናፊ ሆነው የሚመረጡት አመልካቾች/ተወዳዳሪዎች፤

- ከአምስት ሺ እስከ አሥር ሺ የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ የገንዘብ ድጋፍ (መነሻ ካፒታል) ይሸለማሉ፡፡
- ተገምግመው በሚለዩ ክፍተቶች ወይም ፍላጎቶች ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ ስልጠናዎችና የንግድ ስራ ማሳደጊያ አገልግሎቶች ያገኛሉ፡፡
- በቀጣይም አፈፃፀማቸውንና አቅማቸውን መሰረት በማድረግ፤ በአማካይ እስከ 25,000 የአሜሪካን ዶላር ሆኖ እስከ 40,000 ዶላር ለሚደርስ የገንዘብ ሽልማት ለሚያስገኝ ውድድር ሊታጩ ይችላሉ፡፡

<u>የውድድር አማራጭ 1፡</u> የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ፈጠራ ብቻ

| |
|---|
| 1) <u>የፈጠራው ርዕስ (1 ገፅ)</u><br>2) <u>የፈጠራው አጭር ማብራሪያ (ግማሽ ገፅ)</u> |
| 3) <u>ፈጠራው ከተመሳሳይ ቴክኖሎጂዎች አንፃር ልዩ የሚያደርገው (ግማሽ ገፅ)</u> |

4) **ፈጠራው የሚያመጣቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽእኖዎች (ግማሽ ገፅ)**

5) **ፈጠራውን ተግባር ላይ ለማዋል የሚወስደው ጊዜ እና ዝርዝር ተግባራቶች (ግማሽ ገፅ)**

6) **የፈጠራ ዲዛይን እና አሰራር / በፈጠራ ስራው ሊያመጡ የሚችሉትን የተፅእኖ ውጤት ያብራሩ ከሚከተሉት በአንድ ወይም በብዙ መንገድ ተጽዕኖውን ማረጋገጥ ይቻላል (ሁለት ገፅ)**

- የተቆጠበ/የዳነ የጊዜ፣ የጉልበት፣ የነዳጅ ወይም የቁሳቁስ መጠን
- የተቀነሰ የቆሻሻ መጠን
- የተጨመረ/ያደገ ውጤታማነት
- ትርፋማነት፣ የንብረት መጠን፣ እና የድርጅቱ ሰራተኞች ብዛት … ወዘተ

7) **ፈጠራውን ተግባር ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ቁሶች እና ለፈጠራው ግልጋሎት የሚውሉ ቁሶች (ግማሽ ገፅ)**

**ሙሉ መረጃውን ላመግኘት**

8) ፈጠራውን ተግባር ላይ ለማዋል የሚያስፈልገው ዝርዝር የገንዘብ መጠን እና ገንዘቡ እንዴት ሊገኝ እንደታሰበ ማብራሪያ (አንድ ገፅ)

9) በፈጠራው ላይ እስካሁን ፈሰስ የተደረገ የገንዘብ መጠን እና ቅድሚያ ለሚሟሉ ቁሶች የተያዛ የፋይናንስ ምንጭ (ግማሽ ገፅ)

10) ፕሮጀክቱን ለመስራት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን እና የመፍቻ ቴክኒክ/ዘይቤ (ግማሽ ገፅ)

11) ስትራቴጃዊ አቅጣጫዎች (ምርት፣ ሽያጭ፣ ማስፋፊያ፣ ወዘተ) ያያይዙ

12) የማቀድ አቅምዎን የሚያሳይ ሌላ ማንኛውም ዓይነት መረጃ ያያይዙ

13) የፈሰሰው መዋዕለ ንዋይ የሚመለስበት ጊዜ (አንድ መስመር)

14) ቢያሸንፉ ገንዘቡን እንዴት ሊጠቀሙ እንዳሰቡ በደንብ ይግለፁ (ግምሽ ገፅ)

**ስምምነትን ማረጋገጫ**

- ይህን የማመልከቻ ቅፅ ሲሞሉ የሞሉት መረጃ ትክክለኛና በእውነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማረጋገጫ እየሰጡ መሆኑን ይገንዘቡ፡፡
  - በተጠቀሰው ዘርፍ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አምራች መሆኖን ወይም የፈጠራ ባለቤት መሆንዎን
  - የተመዘገበ ህጋዊ ካምፓኒ መሆኑን ማረጋገጥ (የንግድ ምልክት እና ማስረጃ)
  - ፎርሙን እንደመነሻነት መጠቀም የሚችሉ ሲሆን ከ 10 (አስር) ገፅ ከበለጠ ከውድድሩ ይሰራዛል፡፡ ሌሎች ተጨማሪ በፕሮጀክቱ ላይ ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸውን ማለትም የፋይናንስ ማሳያ፣ ሰርተፍኬት፣ ንግድ ፍቃድ፣ ፓተንት፣ ዲዛይን፣ ወዘተ ከ 10 ገፅ ያልበለጠ ያመላክቱ፡፡
  - ፕሮፖዛሉን በአማርኛም ሆነ በእንግሊዘኛ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

✍ ይህንን የማመልከቻ ቅፅ በድህረ ገፃችን (www.mint.gov.et) ላይ ማግኘት የሚችሉ መሆናችን በትህትና እንገልፃለን፡፡

✍ የውድድሩ የማብቂያ ግዜ ሚያዚያ 07 2012 ዓ.ም ይሆናል፡፡

✍ የውድድር ፎርሙን ሞልተው ሲያጠናቁ ፈርመውበት በኢሜል አድራሻችን innovation.research@mint.gov.et ላይ መላክ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

✍ ለበለጠ መረጃ <u>+251118592039/+251920719936/+251911661675/+251913990608/+251912612679 (ሚያዚያ 10 2012 ዓ.ም ብቻ በነዚህ ስልኮች መረጃዎችን ማነጋገር ይቻላል)</u>

## <u>የውድድር አማራጭ 2:</u> የገጠር ኢነርጂ ቴክኒሎጂ ንግድ ስራ ሞዴል ፈጠራዎች ብቻ

1) **<u>የንግድ ስራው ርዕስ</u>**
2) **<u>የንግድ ስራ ሞዴሉን ቁልፍና ልዩ ባህሪያት/ይዘቶች የሚያሳይ (ግምሽ ገፅ)</u>**

3) <u>የንግድ ስራ ሞዴሉን ዓይነት ያመልከቱ (ግማሽ ገፅ)</u>

4) <u>የንግድ ስራ ሞዴሉ የሚያመጣቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ለውጦች ያብራሩ (ግማሽ ገፅ)</u>

5) <u>ከሌሎች የንግድ ስራ ሞዴሎች ልዩ የሚያደርጉትን ነጥቦች ይግለፁ (ግማሽ ገፅ)</u>

6) <u>ለረጂም ጊዜ የማያቋርጥ/ዘላቂነት ያለው ፕሮጀክት መሆኑን ያሳዩ (ግማሽ ገፅ)</u>

7) ***ዕቅድዎ የሚከተሉትን ማሳየት አለበት፡ (ሁለት ገፅ)***

- ዋና/ወሳኝ አቅሞች
- ተቋማዊ አደረጃጀት (ያያይዙ)
- የገንዘብ ዝግጅቶች
- የወጪ ማሳያ (ያያይዙ)
- የገቢ ሞዴል (ያያይዙ)
- ስትራቴጃዊ አቅጣጫዎች (ምርት፣ ሽያጭ፣ ማስፋፊያ፣ ወዘተ)
- የማቀድ አቅምዎን የሚያሳይ ሌላ ማንኛውም ዓይነት መረጃ (ያያይዙ)

8) ***ምን ያህል መነሻ ገንዘብ እንደሚያስፈልገውና እንዴት ሊገኝ እንደታሰበ (ግማሽ ገፅ)***

9) ***ሊከሰቱ የሚችሉ ተግዳሮቶች ካሉና እንዴትስ መፍታት እንደታሰበ (ግማሽ ገፅ)***

10) ***በቅድሚያ መሟላት ያለባቸውን ለመግዛት ምን የፋይናንስ ምንጭ ለመጠቀም ታስቧል (ግማሽ ገፅ)***

| |
|---|
| 11) <u>ታሳቢ የተደረጉ ደንበኞች፣ ከደንበኞች ጋር የሚኖር ግንኙነት (ግማሽ ገፅ)</u> |
| 12) <u>ቢያሸንፉ ገንዘቡን እንዴት ሊጠቀሙ እንዳሰቡ በደንብ ይግለፁ (ግማሽ ገፅ)</u> |

<u>ስምምነትን ማረጋገጫ</u>

- ይህን የማመልከቻ ቅፅ ሲሞሉ የሞሉት መረጃ ትክክለኛና በእውነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማረጋገጫ እየሰጡ መሆኑን ይገንዘቡ፡፡
  - በተጠቀሰው ዘርፍ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አምራች መሆኖን ወይም የፈጠራ ባለቤት መሆንዎን
  - የተመዘገበ ህጋዊ ካምፓኒ መሆኑን ማረጋገጥ (የንግድ ምልክት እና ማስረጃ)
  - ፎርሙን እንደመነሻነት መጠቀም የሚችሉ ሲሆን ከ 10 (አስር) ገፅ ከበለጠ ከውድድሩ ይሰራዛል፡፡
  - ፕሮፖዛሉን በአማርኛም ሆነ በእንግሊዘኛ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
  - ✍ ይህንን የማመልከቻ ቅፅ በድህረ ገፃችን (www.mint.gov.et) ላይ ማግኘት የሚችሉ መሆናችን በትህትና እንገልፃለን፡፡ ሌሎች ተጨማሪ በፕሮጀክቱ ላይ ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸውን ማለትም የፋይናንስ ማሳያ፣ ሰርተፍኬት፣ ንግድ ፍቃድ፣ ፓተንት፣ ዲዛይን፣ ወዘተ ከ 10 ገፅ ያልበለጠ ያመላክቱ፡፡

✍ የውድድሩ የማብቂያ ግዜ ሚያዚያ 07 2012 ዓ.ም ይሆናል፡፡

✍ የውድድር ፎርሙን ሞልተው ሲያጠናቁ ፈርመውበት በኢሜል አድራሻችን innovation.research@mint.gov.et ላይ መላክ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

✍ ለበለጠ መረጃ <u>+251118592039/+251920719936/+251911661675/+251913990608/+251912612679 (ሚያዚያ 01 2012 ዓ.ም ብቻ በነዚህ ስልኮች መረጃዎችን ማነጋገር ይቻላል)</u>

<u>ማሳሰቢያ:</u>

## <u>ለግል አመልካቶች ቅድሚያ መሙዋላት ያለባቸው ጉዳዮች:</u>

☐ አመልካቶች አሁን ሊወዳደርበት በሚያስበው የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ወይም የቢዝነስ ሞዴል የፈጠራ ሥራ በመጀመሪያው የሽልማት ውድድር ተወዳድሮ ተጠቃሚ/አሸናፊ ያልነበረ መሆን አለበት

☐ አመልካቹ የፈጠራ ሥራው ሕጋዊ ባለቤት መሆን አለበት፡፡

☐ አመልካቹ የፈጠራ ሥራው (ለገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ፈጠራ ሥራ) ናሙና (prototype) ሊኖረው የሚገባ ሲሆን በሚጠየቅበት ጊዜም ናሙናውን ማሳየት ወይም ናሙናውን ሠርቶ/አምርቶ ማሳየት የሚችል መሆን አለበት፡፡

☐ የግል አመልካቹ የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ቢገኝ/ቢመረጥ፤ የፈጠራ ሥራውን አምርቶ ለገበያ ለማቅረብ የሚያስችለውን አግባብ ያለውን የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ተቋም/ኢንተርፕራይዝ ለማቋቋም ቁርጠኛ መሆን አለበት፡፡

☐ አመልካቹ ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆን አለበት፡፡

<u>**የግሉ ዘርፍ ተቋማት/ኢንተርፕራይዞች በውድድሩ ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችሉ መስፈርቶች**</u>

☐ ፈጠራው በኢትዮጵያ የገጠሩ ማህበረሰብን የኃይል ችግር ለመፍታት ለሚደረገው ጥረት ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክት መሆን አለበት፡፡

☐ ድርጅቱ/ወይም የድርጅቱ ባለቤት የፈጠራ ሥራው ሕጋዊ ባለቤት መሆን አለበት፡፡

☐ ድርጅቱ በዚህ አሁን ሊወዳደርበት በሚያስበው የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ወይም የቢዝነስ ሞዴል የፈጠራ ሥራ በመጀመሪያው የሽልማት ውድድር ተወዳድሮ ተጠቃሚ /አሸናፊ ያልነበረ መሆን አለበት፡፡

☐ ድርጅቱ በፌዴራል እና/ወይም በክልል ባሉ ለንግዱ ዘርፍ በወጡ ህጎች መሰረት የተመዘገበ መሆን አለበት፡፡

☐ ድርጅቱ ቢያንስ ለ1 አመት ያህል በገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሰራ መሆን አለበት፡፡

☐ ድርጅቱ ሁሉንም ተገቢ የመንግስት ግብር የከፈለ መሆን አለበት፡፡

☐ የድርጅቱ ባለቤትነት (የጥምር ሽርክና ከሆነ ደግሞ የድርጅቱ አብዛኛው የባለቤትነት ድርሻ) የኢትዮጵያዊ/የኢትዮጵውያን መሆን አለበት፡፡